የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኢንፎሜሽንና ኮ/ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከየካቲት 16 - 23ቀን 2018 ዓ.ም
FEBRUARY 23- MARCH 1 / 2026 G.C

1. 4ኛው በኢትዮጵያ ኢንቨስት ያድርጉ ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፎረም መጋቢት 17 እና 18 ቀን 2018 በአዲስ አበባ ይካሄዳል

ኢዜአ፡ የካቲት 24/2018

4ኛው በኢትዮጵያ ኢንቨስት ያድርጉ የኢንቨስትመንት ፎረም መጋቢት 17 እና 18 ቀን 2018 ዓ.ም በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ ተገለጸ።

ፎረሙን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የዓለም ባንክ የጋራ መግለጫ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ዘለቀ ተመስገን(ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ፎረሙ በኮሚሽኑ፣ በገንዘብ ሚኒስቴርና በአጋር የልማት ድርጅቶች ትብብር የተዘጋጀ ነው።

የመድረኩ ዋና ዓላማ አዳዲስ የውጭና የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶችን መሳብ፣ መንግስት ለዘርፉ የሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ማሳየት እንዲሁም በቅርቡ የተደረጉ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ ማሻሻያዎችን ለባለሀብቶች ማስተዋወቅ ነው ብለዋል።

በፎረሙ ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ ታዋቂ ኩባንያዎች፣ የንግዱ ማህበረሰብ መሪዎች፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ አማካሪዎችና የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ አባላት እንደሚሳተፉ ጠቁመዋል።

መገናኛ ብዙኃን የሀገሪቱን የኢንቨስትመንት ዕድሎች በማስተዋወቅና የፎረሙን ስኬት በማብሰር በኩል የሚጠበቅባቸውን ሙያዊ ኃላፊነት እንዲወጡም ጥሪ አቅርበዋል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ሰመሪታ ሰዋሰው በበኩላቸው፤ መንግስት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ሰፊ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻያዎችን ማድረጉን ገልጸዋል።

በሀገሪቱ ባሉ እምቅ አቅሞችና በመንግስት የሪፎርም ስራዎች ምክንያት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ ከፍተኛ መነሳሳት መኖሩን ተናግረዋል።

ይህ ፎረም በእነዚህ ዕድሎች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ትልቅ መድረክ እንደሚሆንም አስረድተዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8415332

2. የቡና ወጪ ንግድን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቷል

ኢዜአ፡ የካቲት 23/2018

የኢትዮጵያን የቡና ወጪ ንግድ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪነቱን ለማሳደግና የቡና አቅርቦት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ትኩረት መሰጠቱን የግብርና ሚኒስትር አቶ አዲሱ አረጋ ገለጹ።

የግብርና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ጋር በመተባበር ከቡና አምራቾች፣ ላኪዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በቡና ወጪ ንግድ አፈጻጸም ዙሪያ ውይይት አካሂዷል።

በውይይቱ ባለፉት ዓመታት በቡናው ዘርፍ የተመዘገቡ ስኬቶችን በመገምገም፣ በቀጣይ ወራት ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ተደርጓል።

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ አዲሱ አረጋ በወቅቱ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ምሰሶ የሆነውን የቡና ዘርፍ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር መንግስት በትኩረት እየሰራ ነው።

ተለዋዋጭ የሆነውን የዓለም ገበያ ታሳቢ በማድረግ የቡና ምርትን በጥራትና ፍጥነት ለገበያ ማቅረብ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ጠቅሰው፤ በቀጣይ ሦስት ወራት በአርሶ አደሮች፣ በአቅራቢዎችና ላኪዎች መጋዘን የሚገኘውን ቡና ጥራቱን ጠብቆ በፍጥነት ለዓለም ገበያ ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑንም አጽንኦት ሰጥተዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8413789

3. ብሔራዊ ባንክ በተለያዩ መተግበሪያዎች የሚደረጉ የአቻ የዲጂታል ግብይቶችን በጊዜያዊነት አገደ

ኤፍ.ኤም.ሲ ፡ የካቲት 20፣ 2018 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ክሪፕቶ ከረንሲን ጨምሮ ፈቃድ በሌላቸው የተለያዩ መተግበሪያዎች የሚደረጉ የአቻ የዲጂታል ግብይቶችን በጊዜያዊነት አግዷል፡፡

ባንኩ ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው÷ በተዘረጉ የቁጥጥር ማዕቀፎች መሰረት በተደረገ ክትትል ግለሰቦች ከባንኩ ፈቃድ በሌላቸው የተለያዩ መተግበሪያዎች ግብይቶችን እየፈፀሙ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ የዲጂታል ግብይት ፍላጎት እየጨመረ በመጣበት በዚህ ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ገልጸ፤ ግለሰቦች ግብይት በሚፈፅሙበት ወቅት በትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርተው ሊሆን እንደሚገባ አሳስቧል፡፡

በተለይም የዲጂታል ግብይቶች የገበያ ተለዋዋጭነትን፣ የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ማሳሳትን፣ የሳይበር ወንጀልን፣ የግብይት ግልፀኝነት ችግሮችን የሚያስከትሉ እንዲሁም የህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር እና የፋይናንስ ሽብርተኝነት ክልከላ ማዕቀፍ የሌላቸው መሆኑን አብራርቷል፡፡

ባንኩ ዲጂታል የግብይት ቴክኖሎጂዎች ደህንነታቸው እንዲጠበቅ የሚያስችል አጠቃላይ የቁጥጥር ማዕቀፍ በመዘርጋት እየሰራ መሆኑን አስገንዝቧል፡፡ በቀጣይም የፋይናንስ መረጋጋትን እና የብሔራዊ የክፍያ ስርዓቱን ታማኝነት ለመጠበቅ ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቆጣጣሪዎች እና ከሀገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት ጋር ቀጣይነት ያለው ምክክር እንደሚደረግ ጠቁሟል፡፡

https://www.fanamc.com/archives/310457

ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን (FDI) በመሳብ ሁለተኛ ደረጃ መያዝ መቻሏን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አስታውቋል።

EBC: ሐሙስ የካቲት 19, 2018

ይህ ታላቅ ስኬት የተመዘገበው በ2016 ዓ.ም የተጀመረውን ታሪካዊ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ ተከትሎ ባለሀብቶች በ ሀገሪቱ የኢኮኖሚ ምኅዳር ላይ ያላቸው እምነት በማደጉ ነው።

በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ደግሞ ለ2 45 አዳዲስ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል። በዓመቱ መጨረሻ 5.17 ቢሊዮን ዶላር ለማስገኘት የታቀደው ግብ አፈጻጸም አበረታች ደረጃ ላይ ይገኛል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ የውጭ ምንዛሪ በገበያ እንዲመራ መደረጉ፣ የመሠረተ ልማት መስፋፋት እና የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ለታዳሽ ኃይል አቅርቦት ያለው ሚና የዓለም አ ቀፍ ኩባንያዎችን ፍላጎት በእጅጉ ጨምሮታል።

https://www.ebc.et/Home/NewsDetails?NewsId=4346

5. AfCFTA Heralds Significant Opportunities for Ethiopia, Regional Business Communities: ECCSA

ENA: February 28, 2026

The African Continental Free Trade Area (AfCFTA) will bring significant opportunities not only for Ethiopia and the business community but also for other African countries, Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) Secretary-General told ENA.

Africa is a continent of more than 1.57 billion people, with a predominantly young population and the continent's total GDP exceeds 3.4 trillion USD, making it a vast and preferred market for business.

ECCSA Secretary-General Kenenissa Lemie said the African Continental Free Trade Area (AfCFTA) is a major gateway for local traders into the large market of the continent.

AfCFTA offers substantial benefits to Ethiopian traders, providing an expansive opportunity to sell products across all of Africa, rather than being confined to the domestic market. As trade follows free-market principles, it would enable the provision of goods and services without tariffs or trade barriers, he stated. Moreover, the free competition within the zone would encourage traders to constantly improve themselves and adopt new practices, fostering a more active and effective business environment, the Secretary-General added.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_8400065

6. Ethiopia Targets Over $2.4 Billion In Deals As 4th 'Invest In Ethiopia' Forum Set For March 26-27

FMC: March 3, 2026

Ethiopia is seeking to secure more than 2.4 billion U.S. dollars in new investment commitments during the Fourth "Invest in Ethiopia 2026" Forum scheduled for March 26–27, 2026, in Addis Ababa. The high-level forum, to be held at the Skylight Hotel under the theme "Ethiopia is Ready for Investment," is being organized by the Ethiopian Investment Commission in collaboration with the Ministry of Finance and international development partners. At a joint press briefing held today, Chief Commissioner of EIC Zeleke Temesgen said Ethiopia currently ranks second in Africa in foreign direct investment (FDI) inflows, describing the forum as a central instrument in the country's strategy to position itself among the continent's leading investment destinations.
https://www.fanamc.com/english/ethiopia-targets-over-2-4-billion-in-deals-as-4th-invest-in-ethiopia-forum-set-for-march/

7. Ethiopian Airlines Suspends Middle East Flights

The Reporter: February 28, 2026

Ongoing strikes and security concerns have pushed Ethiopian Airlines to cancel flights to and from several Middle Eastern destinations.
Routes affected include Amman, Tel Aviv, Dammam, and Beirut.
The disruption comes as years of tension between Israel and Iran boil over into an all-out conflict. Israel and the US began striking this morning, and Tehran has hit several US military bases in the region in retaliation.
"We continue to actively monitor developments and will take appropriate measures to ensure the safety and convenience of our passengers and crew," reads a statement issued by Ethiopian.
https://www.thereporterethiopia.com/49519/

8. NBE to Launch Interdealer FX Platform, Ease Export Surrender Rules Under Reform Drive

The Reporter: March 1, 2026

As part of its ongoing macroeconomic and foreign exchange reforms, the National Bank of Ethiopia (NBE) plans to establish an interdealer trading platform and relax surrender requirements for commodity exporters by the end of the current fiscal year.
The interbank foreign exchange market was officially launched on January 28 through a technology-backed system operating on the trading infrastructure of the Ethiopian Securities Exchange (ESX), which features a dedicated FX segment. While the platform is designed to ensure transparency, competitive pricing, and real-time execution, its performance so far remains unclear.
Building on this launch, the central bank is preparing a roadmap to deepen the interbank FX market. According to commitments made to development partners, the roadmap will include the creation of an interdealer trading platform—an electronic system enabling anonymous, real-time trading among major financial institutions.
This initiative is a key structural benchmark under the reform program introduced at the start of the 2024/25 fiscal year. The NBE aims to operationalize the new platform by the first quarter of 2026/27.
Officials say a well-functioning interbank market will strengthen banks' foreign exchange risk management and enhance transparency. Work is also underway to upgrade the settlement system so that interbank FX transactions can be settled domestically.
Interdealer platforms serve as the backbone of modern interbank FX markets. By aggregating liquidity from multiple banks into a single high-volume marketplace, they improve pricing efficiency, liquidity, and operational stability. Banks can also hedge inventory imbalances from customer transactions more quickly, reducing market risk exposure.
https://capitalethiopia.com/2026/03/01/nbe-to-launch-interdealer-fx-platform-ease-export-surrender-rules-under-reform-drive/